CancerCare Manitoba
CervixCheck

## የፓፕ ምርመራ ምንድነው?

የፓፕ ምርመራ በማህፀን በር (cervix) ላይ የሚታዩ የማይጠበቁ ለውጦችን ያሳያል። የታዩ ለውጦችን በጊዜ ማከም የማህፀን በር ነቀርሳን ይከላከላል። የፓፕ ምርመራ ነፃ ነው።



## የማህፀን በር (cervix) ምንድን ነው?

የማህፀን በር በማህፀን በታችኛው ክፍል የሚገኝ ቀዳዳ ነው። ልጆች ሲወለዱ የሚወጡት በማህፀን በር ነው።




## የማይጠባቁ ለውጦች መነሻው ምንድነው?

ሂይማን ፓፒሎማ ቫይረስ ወይም ኤችፒቪ (HPV) የሚባለው በግብረሥጋ ግንኙነት አማካኝነት በቀላሉ የሚተላለፈው ቫይረስ በሴት የማህፀን በር ላይ የማይጠበቁ ለውጦችን ሊያስከትል ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በኤችፒቪ አማካኝነት የሚታዩት ያልተጠበቁ ለውጦች ነቀርሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ። የፓፕ ምርመራ እነዚህን ያልተጠበቁ ለውጦች ነቀር ከመሆናቸው በፊት ሊያገኛቸው ይችላል።

## የፓፕ ምርመራዎች ያስፈልጉኛል?

ግብረሥጋ (የግብረሥጋ ግንኙነትና ወሲባዊ መነካካት) አድርገው የሚያውቁ ሴቶች ሁሉ የፓፕ ምርመራዎች ማድረግ ይገባቸዋል።

## የፓፕ ምርመራ በየምን ያህል ጊዜ ማድረግ ይገባኛል?

እድሜዎ 21 ዓመት ከሞላ ጀምሮ በየ 3 አመት አንዴ የፓፕ ምርመራ አድርጉ ይህ ምርመራ 69 ዓመት እስኪሞላዎ ድረስ መቋረጥ የለበትም

## የኤችፒቪ (HPV) ክትባት ምንድነው?

የኤችፒቪ ክትባት የማህፀን በር ነቀርሳ ከሚያስከትሉ ከተወሰኑ የኤችፒቪ ዓይነቶች የሚከላከል ክትባት ነው። ክትባቱ ቀደም ብለው በኤችፒቪ የተያዙትን አያክምም። ክትባት ያደረጉ ቢሆንም ተከታታይ የፓፕ ምርመራ ማድረግ ይኖርብዎታል።

## የፓፕ ምርመራ ለማድረግ የት መሄድ አለብኝ?

ሃኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ፤ የአካባቢዎን የጤና ማዕከል ይጎብኙ፤ ወይም ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ።
GetCheckedManitoba.ca

**ሴቶች ተከታታይ የፓፕ ምርመራ በማድረግና ያልተጠበቁ ለውጦችን ለማየት እንዲቻል የክትትል ምርመራ ቢያደርጉ አብዛኛውን የማህፀን በር ነቀርሳ መከላከል ይቻላል።**


## ለተጨማሪ መረጃዎች ከማኒቶባ የማህፀን በር ነቀርሳ

**CervixCheck, CancerCare Manitoba**
**#5-25 Sherbrook Street**
**Winnipeg, Manitoba R3C 2B1**

ስልክ: (204) 788-8626
ነፃ ስልክ: 1-866-616-8805
CervixCheck@cancercare.mb.ca
GetCheckedManitoba.ca



*Amharic, 2017*